# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 238 ህዳር 27 2005 ገጽ 1


ወያኔ ከሰሞኑ ያደለዉ የስልጣን ራሺን አህዴድ ዉስጥ የተነሳዉን የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ያፈነ ከመሰለው እጅግ በጣም ተሳስቷል። ይልቁንም ይህ የስልጣን ረሺን የሚያሳየዉ ይህ ከእያንዳንዱ ድርጅት የተውጣጣዉ የጠቅላይ ሚንስትርነት ድሪቶ መአት ለሀገሪቱ ፈረስ እንሰራለን ብለው ግመል እየሰሩ መሆናቸውን ነዉ። የይህ በዚህ በኮሚቴ በተሰራ ግመል አይሉት ፈረስ ደግሞ አህዴድም ሆነ ሌሎቹ ወያኔ ሰራሽ ድርጅቶች አይታለሉም ብለን እናምናል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በእብሪተኛው የወያኔ አገዛዝ የተፈናቀሉ ኢትዮጵያዊያን ከሁለት ሰው በላይ ሆነው ማውራት ተከለለከሉ

በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ጎጆ ቀልሰው ከሚኖሩበት ሰፈር ህገወጦች ናችሁ በሚል ሰበብ በማንአለብኝነት እብሪት በተወጠረው ወያኔ ትእዛዝ ጎጇቸው ፈርሶ እንዲፈናቀሉና ሜዳ ላይ እንዲወድቁ የተደረጉት ዜጎች በሀገራችን መኖር ካልቻልን ወደ ሌላ ሀገር ሄደን በስደተኝነት ለመኖር እንችል ዘንድ ሁኔታዎች ይመቻቹልን ማለታቸው ተሰማ።

ተፈናቃዮቹ በየአካባቢዎቹ በመዘዋወር ላነጋገራቸው የግንቦት 7 ዘጋቢ ሲገልጹ ህገወጡ ወያኔ ህጋዊ ሰነድ ይዘን ህገወጦች ናችሁ ይለናል በጣም የሚገርም ነው፤ ሌላው ቀርቶ በህገ ወጥ መንገድ የሰፈሩ አንዳንድ እንኳን ቢኖሩ ሃላፊነት የሚሰማው መንግስት ቢሆን ኖሮ አስቀድሞ መጠለያ በማዘጋጀት ሊያዛውራቸውና መሬቱን ሊጠቀምበት ይችል ነበር።ነገር ግን ለዜጎች አንዳችም ደንታ የሌለው ዘረኛውና ስግብግቡ ወያኔ ማንንም ከማንም ሳይለይ ከመሬቱ የሚያገኘውን ጥቅም ብቻ በመመልከት ቤቶቻችንን በላያችን ላይ በማፍረስ ሜዳ ላይ ጥሎናል ብለዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ትግላቸውን ቀጥለዋል፣ አሁንም መብታችን ይከበር በማለት እየጮሁ ነው

ከአስራ አንድ ወራት በላይ በዘረኛውና ግፈኛው የወያኔ አምባገነን አገዛዝ ሃበሳቸውን እያዩ ያሉት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ተቃውሞአቸን ማሰማት ቀጥለዋል። በትናንትናው እለት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩት በታላቁ የአንዋር መስገድ በመገኘት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ እየተከተለ ያለውን ፖሊሲ አውግዘዋል።

እነኝህ ኢትዮጵያዊያን 27 ቁጥር የተጻፈበት ወረቀት በማውለብለብ "አንቀጹ ይከበር፣ ኮሚቴዎቻችን ይፈቱ፣ አሸባሪዎች አይደለንም" በማለት አኑዋር መስጊድ ላይ ድምጻቸውን በከፍተኛ ሁኔታ ሲያስተጋቡ ውለዋል።

ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ሙስሊሞች ውስጥ አንዳንዶችን አነጋግሮ ባገኘው ምላሽ፣ ምንም ይሁን ምን፣ የወሰደውን ጊዜም ቢወስድና፣ መስዋእትነትንም ቢያስከፍልም፣ እኛ መብታችንን ሳናስከብር ፍጹም ትግላችንን አናቆምም፣ እናም የኢትዮጵያ ህዝብ ከጎናችን እንዲቆም ጥሪ እናደርጋለን ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## በፍርሃት ድባብ የተዋጠው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በባህር ዳር አካባቢ ከፍተኛ ፍተሻ እያደረገ ነው

በኢትዮጵያዊያን ላይ እያደረሰ ያለውን ግፍና በደል በማዘናጋት ተግባር ላይ ተጠምዶ የሚገኘው ዘረኛ አገዛዝ በቅርብ ቀን ይከበራል ያለውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን በአል አክብሩ በሚል አስገዳጅ ትእዛዝና ክትትልም በየመስሪያ ቤቶች እየተካሄደ ሲሆን በባህር ዳር ከተማ የሚከበረውን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን ተከትሎ ወደ ባህር ዳር የሚገቡ ንፁሀን ዜጎችን በሁለቱም የተሽከርካሪ መግቢያዎች እና በአውሮፕላን የሚገቡትን በፍተሻ እያጨናነቀ፣ ነፃነታቸውን በእጅጉ እየገፈፈ እና ህዝቡን ከመንገዱ እያስተጓጎለ እንደሚገኝ ይገኛል በማለት ነዋሪዎች ገልጸዋል።

በፍርሃት አለንጋ እየተገረፈ ያለው የወያኔ አገዛዝ "የአይናችሁ ቀለም አያምርም" በሚል አይነት ሰበብ ዜጎችን እንደፈለገው ወደ እስር ቤት እያስገባ መሆኑንም ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ይህ በንዲህ እንዳለ በትግራይ ክልል ህወሀትን አትደግፉም የተባሉ ዳኞች እየታሰሩ ነው ሲል የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘግቧል። እንደ ኢሳት ዘገባ በትግራይ ክልል ዳኞች ላይ ከፍተኛ ግምገማ በመካሄድ ላይ ሲሆን አመለካከታቸው ከመለስ ራእይ ውጭ ነው የተባሉ ዳኞች ተይዘው ታስረዋል ብሏል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በክልሉ የሚገኙ መምህራንም በሚታየው የመብት አፈና እየተማረሩ መምጣታቸውን ኢሳት ገልጿል።

## የወያኔ ፌደራል ፖሊስ በዩኒ ቨርሲቲው ቅጥር ግቢ በመግባት የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን ደበደበ

በጂማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላነሷቸው የመብት ጥያቄዎች እንደተለመደው የጨካኙ ወያኔ አገዛዝ ፌድረአል ፖሊሶች ዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ድረስ በመግባት ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ተማሪዎች በቆመጥ መደብደባቸዉን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የሚገኝ ምንጮችን በመጥቀስ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በላከልን ዜና አመለከተ። የጂማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጥያቄዎቻችን ይመለስልን በሚል ለዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆንም ለጥያቄአቸው ተገቢ ምላሽ ሳይሆን የ ጠበቃቸው የወያኔ ፌደራል ፖሊሶች ዱላ መሆኑን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጿል። ተማሪዎቹ በዋናነት ካነሷቸው ጥያቄዎች በዋነኛነት የምንማረው ትምህርት ጥራት በጣም የወረደና ደረጃንም ያልጠበቀ በመሆኑ ሊስተካከል ይገ ባል፡ የሚል እንደሆነ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

በዚሁና ተያያዥ በሆኑ የመብት ጥያቄዎች ምክንያት የወያኔ ፌደራል ፖሊሶች ዩኒ ቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ገብተው ተማሪዎችን ደብድበዋል፣ መስኮቶችም ተሰባብረዋል፡፡ ከዚሁ የወያኔ አገዛዝ መረን የለቀቀ ተግባር ጋር በተያያዘ ተማሪዎችም ቁጣቸው እየጨመረ መሄዱ የታወቀ ሲሆን በተመሳሳይ መልኩ ይህ ጥያቄ በወልቂጤና ነቀምት ዩኒ ቨርሲቲዎች በመቀጣተል ላይ መሆኑን ዘጋቢያችን ገልጿል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የብሄር ብሄረሰቦች ቀን የወያኔ ድራማ ነው፡ ሲሉ አስተያየት ሰጪዎች ገለጹ

ኢትዮጵያዊያንን የተለያዩ አጀንዳዎች በማስጨበጥ ግፍና በደሉን በማረሳሳት ሙከራ ላይ የተጠመደው የወያኔ አገዛዝ አሁንም የብሄር ብሄረሰቦች ቀን የሚል ነጠላ ዜማ ለቆ ኢትዮጵያዊያን መቆሚያና መቀመጫ እንዲያጡ እየደረገ መሆኑን ዘጋቢያችን በተለያዩ የሃገሪት ክፍሎች የሚገኙ ዜጎችን ዋቢ በማድረግ ገለጸ። ዘጋቢያችን አንድ በጂማ ዩኒቨርሲቲ የሚገኙ ምንጭን በመጥቀስ እንደዘገበው በጂማና አካባቢዋ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የብሄር ብሄረሰቦች ቀን የወያኔ ድራማ ነው፣ እኛ አንቀበለውም፣ በ አሉንም በምንም አይነት ፈቃደኝነት አናከብረውም ማለታቸው ታዉቁአል።

ዘረኛው የወያንኔ አገዛዝ በቀጣዩ ቅዳሜ የብሄር ብሄረሰቦች በአል በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች እንዲከበር እያስገደደና ደፋ ቀና እያለ የሚገኝ ሲሆን በሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን በሚደረገው አሰልቺ ተግባር ሁሉ መሰላቸታቸውንና ወያኔም ድራማ የማያልቅበት ማፊሪያ አገዛዝ መሆኑን ገልጸዋል።

ዘጋቢያችን በለቀምት ነዋሪ የሆኑ አንድ ግለሰብን በስልክ ያናገረ ሲሆን እንደግለሰቡ ምላሽ፣ ወያኔ ለምን በንዲህ አይነት ድራማ እንደተጠመደ ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልጽ ነው፣ ኢትዮጵያዊያን የሚያነሷቸውን የመብት ጥያቄዎች ለማፈንና ለማዘናጋት ነው። ተወደደም ተጠላ አንድ ቀን አንድ ነገር መሆኑ አይቀርም። እስከዚያው ግን ያለን ምርጫ ሁላችንም በተጠንቀቅ መጠበቅ ነው ማለታቸውን ገልጿል።

## የለገጣፎ ነዋሪዎች እኛ ያልመረጥነው ከንቲባ አያስተዳድረንም ማለታቸው ተዘገበ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን በዘገባው እንዳመለከተው ከመሬት ዝርፊያ ጋር በተያያዘ የከተማው ነዋሪ ያሰማውን ከፍተኛ ተቃውሞ ተከትሎ በቅርቡ ከንቲባውን መገርሳ ገለታን ጨምሮ 5 የካቢኔ አባላትን ከስልጣን ያወረደው የወያኔ አገዛዝ፣ ከአካባቢው ህዝብ ያልተመረጠ አዲስ ከንቲባ በመሾም ለህዝቡ ለማስተዋወቅ የጠራው ስብሰባ በህዝቡ ተቃውሞ እንዲበተን ተደርጓል።

ኢሳት እንደዘገበው ህዳር 21 ቀን 2005 ዓም ከፍተኛ የኦህህዴድ ባለስልጣን የሆነው ቀነአ ኩማ የለገጣፎ ለገዳዲን ህዝብ በመሰብሰብ አዲስ ተሾሞ የመጣውን አለማየሁ ውለታ የተባለዉ ከንቲባ ለማስተዋወቅ ሲሞክር፣ ህዝቡ " ከንቲባ የሚመረጠው ከምክር ቤት ነው፣ ምክር ቤቱን የመረጥነው ደግሞ እኛ ነን፣ እናንተ ያመጣችሁልን ከንቲባ እኛ ያልመረጥነውና ሌላ አካባቢ የሚሰራ ነው፣ ባልመረጥነው መሪ አንደራደርም ባልመረጥነው መሪም አንመራም።" በማለት ተቃውሞ አሰምቷል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ደሮን ሲያታልሏት... በመጫኛ ጣሏት

በወያኔ/ኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረዉ የስልጣን ክፍፍል የፈጠረዉ የእርስ በርስ ሽኩቻ እያየለ መጥቶ ዛሬ አራቱ የእህአዴግ ድርጅቶች ካለመተማመናቸዉ የተነሳ እንኳን አገር መምራት ትናንሽ የፖሊሲ ዉስኔዎችንም በጋራ መወሰን አቅቷቸዋል። “የማይተማመን ባልንጀራ በየወንዙ ይማማላል” እንደሚባለዉ አህዴድ፤ ብአዴን፤ ደኢህዴግና ህወሀት ሁሉም ጠ/ሚኒስቴርና ሁሉም ምክትል ጠ/ሚኒስትር መሆን በመፈለጋቸዉ ቦታዉ አልበቃ ሲላቸዉ እራሳቸዉ የጻፉትን ህግመንግስት ደፍጥጠዉ ከሰሞኑ ሦስት ምክትል ጠ/ሚኒስትር በመሾም አገራችን ኢትዮጵያን የሞኞች ድራማ መድረክ አድረገዋታል። ህዝብንና አገርን ያታለሉ እየመሳለቸዉ በተጨባጭ ግን እራሳቸዉን የሚያታልሉት የወያኔ ባለስልጣኖች እራሳቸዉ ጽፈዉ “ህገመንግስት” ብለዉ የሰየሙትን ከፍተኛዉን የአገሪቱን ህግ ጥሰዉ በታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ አንድ አገር በአንድ ጠ/ሚኒስትርና በሦስት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች እንዲመራ አድረገዋል።

ሰሞኑን በወያኔ መንደር የታየዉ በሹመት መንበሸበሽ ወያኔዎች ሊነግሩን እንሚፈልጉት ከልማትና ከእድገት ጋር ምንም ግንኙነት የዉም። ወያኔ ጠ/ሚኒስትር ከሾመ ከ3ወር በኋላ ሌሎቸ ሁለት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች የሾመዉ በአራቱ አሻንጉሊት ድርጅቶች መካከል የኃ?ማሪያም ደሳለኝን ሹመት ተከትሎ የተፈጠረዉን ኩርፊያና የስልጣን ሽሚያ ለማርገብ አንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም። በተለይ በአገሪቱ ዉስጥ የሌለ የስልጣን መዋቅር ተፈልጎለት ምክትል ጠ/ሚኒስት ሆኖ የተሾመዉ የሙክታር ከድር ሹመት ስራ እንዲሰራበት ሳይሆን “ብዙሀኑን ያለቀፈ ዲሞክራሲ ድሞክራሲ አይደለም” በሚል መርህ ዙሪያ ተሰባስበዉ የዉስጥ ለዉስጥ ትግል የጀመሩትን የኦህዴድ አባላት ለማግባባት ነዉ። ሆኖም ትክክለኛዉን የነፃነት ትግል የጀመሩት የኦህዴድ አባላት እንደዚህ አይነቱን “ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት” የሚሉትን የወያኔ የማጭበርበሪያ ሽፋን ተገንዝበዉ የኦሮሞ ህዝብ የማማባበያ ሳይሆን የትክክለኛ ስልጣን ባለቤት እስኪሆን ድረስ ትግላቸዉን ይቀጥላሉ የሚል የፀና እምነት አለን።

ወያኔ ከሰሞኑ ያደለዉ የስልጣን ራሺን አህዴድ ዉስጥ የተነሳዉን የስልጣን ይገባኛል ጥያቄ ያፈነ ከመሰለው እጅግ በጣም ተሳስቷል። ይልቁንም ይህ የስልጣን ረሺን የሚያሳየዉ ይህ ከእያንዳንዱ ድርጅት የተውጣጣዉ የጠቅላይ ሚንስትርነት ድሪቶ መአት ለሀገሪቱ ፈረስ እንሰራለን ብለው ግመል እየሰሩ መሆናቸውን ነዉ። የይህ በዚህ በኮሚቴ በተሰራ ግመል አይሉት ፈረስ ደግሞ አህዴድም ሆነ ሌሎቹ ወያኔ ሰራሽ ድርጅቶች አይታለሉም ብለን እናምናል።

ወያኔ ህግመንግስታዊ ስርአቱን በኃይል ለመናድ አገኘኋቸዉ እያለ ስንት ሰላማዊና ህግ አክባሪ ዜጎችን ወደጨለማ ቤት እንደወረወሯቸው የሚያዉቀዉ አባት፤እናት ወይም ልጅ የታሰረበት ቤተሰብ ብቻ ነዉ። ወያኔ ህግመንግስቱን የሚጠቀመዉ ተቃዋሚዎቹን ለማጥቃት ነዉ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ወያኔ እሱ እራሱ የጻፈዉን ህግመንግስት ሲያሰኘዉ ይለዉጠዋል፡ የደፈጥጠዋል ወይም ህገመንግስቱ የማይፈቅድለትን ነገር ያደርጋል እንጂ አንድም ቀን ህገመንግስቱን አክብሮ አያዉቅም። ለምሳሌ ባለፈዉ ሳምንት የሾማቸዉ ሁለት ምክትል ጠ/ሚነስትሮች በአገሪቱ ህግመንግስት የኒፈቅዳቸዉ ሹመቶች አይደሉም፤ ሆኖም ወያኔ እርሱን ከህግ በላይ አደርጎ ስለሚያይ ያሰኘዉን ይሾማል ያላሰኘዉን ደግሞ ስላልወደደዉ ብቻ ይሽረዋል።

ለዚህም ነው በወያኔ/ህወሃት ሀገራችን ኢትዮጵያ እየደረሰባት ያለውን ውርደትና እንግልት በመቃወም ስልጣን የህዝብ እንጅ የጥቂት አምባገነኖች አይደለም በሚል ታጥቀን ይህ አካል ለህግ ተገዥ እንዲሆን ማስገደድ ወይም ማስወገድ አለብን የምንለው። አገራችን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ስልጣንን ለብሄር ብሄረሰቦች በኮታ ማደል ሳይሆን እያንዳንዱ ዜጋና እያንዳንዱ ብሄረሰብ መብቱና ነጻነቱ ተከብሮ እራሱን በእራሱ እንዲያስተዳድር ማድረግ ነዉ። ለዚህ ደግሞ ብቸናዉ መፍትሄ በህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት መገንባት ነዉ።

የኢትዮጵያን ህዝብ ለስልጣን አበቃነዉ እያሉ የሚፏልሉት የወያኔ ዘረኞች ዛሬ እነሱ እራሳቸዉ ከፈጠሯቸዉ አሻንጉሊት ድርጅቶች ጋር የስልጣን ሽሚያ ዉስጥ የገቡት የአገሪቱን የጦር ኃይሎች፤ ፖሊስ ሰራዊት፤ የደህንነትና የኤኮኖሚ ተቋሞች ሙሉ በሙሉ እየተቆጣጠሩ ነዉ። የወያኔ ፍላጎት አንድ ነዉ፤ እሱም ስልጣን አለበት የተባለውን ቦታ ሁሉ ረግጠዉ መቆጣጠርና ሌላዉን ህዝብ ተከታይ ማድረግ ነዉ። አህዴድ፤ ብአዴንና ደኢህዴን እነሱ ብዙሃን ሆነዉ ሳለ ከሃያ አመት በላይ የወያኔ ተከታይ ሆነዉ ኖረዋል። ከአሁን በኋላ ግን ቁጥራቸዉንና የሚወክሉትን ህዝብ በሚመጠን መልኩ የፖለቲካ ስልጣን ካልጨበጡ ከወያኔ የኪራይ ቤት ወጥተዉ የራሳቸዉን ቤት መስራት አለባቸዉ። ከአሁን በኋላ ለአህዴድ፤ ለብአዴን፤ ለደኢህዴንና ለህወሀትም በሆን ልህልዉናቸዉ የሚበጃቸዉና ከታሪክ ተጠያቂነት የሚያድናቸዉ ከዚህ ሃያንድ አመት ሙሉ ከተጓዙበት አጥፊና አዉዳሚ መንገድ ወጥተዉ ኢትዮጵያ ዉስጥ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ስርአት ገንብተዉ የበደሉትን ህዝብ መከስ ነዉ።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

.................................................................................................................................

## የወያኔ ፌደራል ፖሊስ በዩኒ ቨርሲቲው ቅጥር ግቢ በመግባት የጅማ ዩኒቨርሲቲ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚሁ ዘገባ ጋር በተያያዘ ዓንድ ስሙ እንዳይገለጽ የጠየቀ የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ለዘጋቢያችን እንደገለጸው ወያኔ በ2004 ዓ.ም ባካሄደው የዩኒቨርሲቲዎች ጉባኤ ላይ ጅማ ዩኒቨርሲቲ በትምህርት ጥራት አንደኛ ደረጃ ላይ ይገ ኛል በሚል እንዲመረጥ አድርጎ የነበረ ሲሆን በትምህርት ጥራት አንደኛ ተብሎ ተመረጠ ዩኒቨርሲቲ ላይ ይህ ጥያቄ መነ ሳቱ ችግሩ ምን ያህል ስር የሰደደ እንደሆነ እና የ ወያኔ ድራማ ምን ያህል እየ ተጋለጠ ለመሆኑ ታላቅ ማሳያ ነ ው፡ በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በአንዳን ዩኒቨርሲቲዎች አንድም የቤተ መጽሃፍና የላብራቶር አገልግሎት ሳይኖራቸው ተማሪዎች ገብተውና ምንም እውቀትን ሳይቀስሙ እንዲመረቁ በማድረግ ተግባር ላይ ተጠምዶ እንደሚገኝ ቀደም ብሎ መዘገቡ ይታወሳል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያዊያን ላይ እያደረሰ ያለው ግፍና በደል መጠኑን ካለፈ እጂግ በርካታ ዓመታት ያለፉ ሲሆን፣ በተለይም ባሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በድንገት ምን ሊፈጠር እንደሚችል መገመት የሚያዳግት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ዘገባዎች እያመለከቱ ነው። የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ከታዋቂው የኢኮኖሚክ ባለሙያ ፐ/ር በፈቃዱ ደግፌ ባደረገው ቃለምልልስ የወያኔ አገዛዝ የህዝብን ብሶት አልሰማ በማለቱ አንድ ቀን ያልጠበቀው አደገኛ ሁኔታ ሊፈጠርበት እንደሚችል ማስጠንቀቃቸው ታውቋል። ዶር በፈቃዱ በቃለ ምልልሳቸው "ህዝቡ የሚሄድበት ቦታ አጥቷል፣ ብሶታል" ያሉ ሲሆን ከአረብ አብዮት የምንማረው ህዝብ መሪ ሳያስፈልገው በብሶቱ ብቻ ሆ ብሎ ሊነሳ የሚችል መሆኑን ነው ሲሉ ገልጸዋል። ፐ/ር በፈቃዱ ደግፌ በቃለ ምልልሳቸው ባሁኑ ሰአት የኢትዮጵያ ባለቤት የኢትዮጵያ ህዝብ ሳይሆን ወያኔ ኢህአዴግ ነው ያሉ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለሙስና ስራ መስራት እንደማይቻል ገልጸዋል።

.................................................................................................................................

## ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ትግላቸውን ቀጥለዋል፣ አሁንም መብታችን ይከበር

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ክልሎች የሚገኙት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ያነሱትን የመብት ጥያቄ ለማፈን በቆመጥ ከመደብደብና እያፈሰም ወደ እስር ቤት ከማጎር በዘለለ እጂግ በርካታ ማስፈራሪያዎችና ማስጠንቀቂያዎች ቢሰጥም ሙስሊሞቹ በአቋማቸው በመጽናት የዘረኛውን የወያኔ አገዛዝ እንቅልፍ ነስተውት እንደሚገኙና ጉዳዩም ለአለም ህዝብ ይፋ እንደሆነ በተደጋጋሚ መዘገቡ ይታወቃል።

## የነቢዩ እንባ

ኢትዮጵያ . . . . ኢትዮጵያ . . . ስሚኝ አንቺ ኢትዮጵያ . . . . አንዳንዴ ቁጭ ብዬ ሳስብ እርቆኝ ሄዷል፤ ሞቷል ወይም አይጠቅመኝም ብለሽ የምታስቢ ይመስለኛል። ተሳስተሻል እናቴ ! ኖሬም ሞቼም እናቴ አንቺዉ ነሽና እባክሽን ስሚኝ ብዙ የምነግርሽ ነገር አለኝ። አዎ! ኢትዮጵያዬ ገና በልጅነቴ ሳልጠግብሽ ሳትጠግቢኝ ተሰናብቼሻለሁ፤ ግንኮ . . . ግንኮ በቅተሽኝ አይደለም ኢትዮጵያዬ ጠልቼሽም አይደለም። የልጅነት ግንባሬን ለአግአዚ ጥይት የሰጠሁት የልጆችሽ ህይወት ከህይወቴ በልጦብኝ በእኔ ሞት እነሱ እንዲኖሩ ነዉ እንጂ አለዚያማ. . . . አለዚያማ እኔም ዛሬ ወደታች ጎንበስ ብዬ ባየሁሽ ቁጥር እንደሚታዩኝ የሂሊና ደሃዎች ሲጎትቱኝ እየተጎተትኩ ሲሉኝ እየሄድኩ ሲያስሩኝ እየታሰርኩ መኖር እችል ነበር። ግን . . . . ግን አሁንም እንደገና መሞት ካለብኝ እሞታለሁ እንጂ ኢትዮጵያዬ አንቺን ከድቼ በአንቺ ዶልቼስ አልኖርም። አባቴም ሆነ አሁን ድረስ የምታለቅሰዉ እናቴ ይህንን አላስተማሩኝም።

እርግጠኛ ነኝ ኢትዮጵያ የዛሬ ሰባት አመት ስንለያይ የገባሽልኝን ቃል የምትረሺዉ አይመስለኝም። አይዞሽ እኔም አልረሳሁም። እኔማ ልርሳዉ ብልም የሰማይ በር በተከፈተ ቁጥር የሚገባዉ ሰዉ ሁሉ የሚያስታዉሰኝ አንቺን ብቻ ነዉና ልረሳዉ አልቻልም። ስሚኝ ኢትዮጵያ. . . ሞቴ ሞትሺን መስዋእትነቴ ስደትሺን ያቆመዉ መስሎኝ ነበር። ምነዉ . . . . .ምነዉ አመድ አፋሽ አረግሺኝ ኢትዮጵያ! ሞቴን ዋጋ አሳጣሺዉ መስዋእትነቴን ባዶ አስቀረሺዉ። አንደ ህልም ጋላቢ ፈረሰኛ ዘለልኩ እንደ ምኞት ተጓዥ መንገደኛ ባከንኩ፤ ሞቼ ላላድንሽ በከንቱ ግንባሬን ለአግአዚ ገበርኩ። ኢትዮጵያ አረ ኢትዮጵያ ምነዉ ልጅሽ ላንቺ ከመታገል ባዕድ አገር መሄድን መረጠ። እግዚኦ በይ . . . እግዚኦ በይ ኢትዮጵያ ልጅሽ ከትግል እየኮበለለ በየባህሩ ሰመጠ፤ ከነፃነትሽ ህይወቱን ከአንድነትሽ ድሎቱን መርጦ ለባዕድ እጁን ሰጠ። ቀና በይና ጉድሺን ተመልከቺ ኢትዮጵያ የወያኔን ጭካኔ ያመለጠ እየመሰለዉ በየባህሩና በየዉቅያኖሱ ያንኑ የፈራዉን ሞት እየጨለጠ አጠገቤ የሚመጣዉ ልጅሽ ቁጥር በረከተ። በተለይ እዚህ ሰማይ ቤት ላለነዉ ሞት የሚሉት መርገም ያንቺ ልጆች ብቻ እየተበደሩ የሚከፍሉት ዕዳ ነዉ የሚመስለዉ። ምንድነዉ ችግሩ ኢትዮጵያ? ደሙን አፍስሶ ቤዛ የሚሆንሽ ልጅ አጣሽ ወይስ እኔዉ ነኝ ሞኙ ለወያኔ ሰግጄ መኖር ስችል ሞቴን የመረጥኩት? ንገሪኝ ኢትዮጵያ . . . አንቺ ነሽ አኔ . . . . ማናችን ነን ቃላችንን ያጠፍነዉ?

አስኪ ላስታዉስሽ እናት አገር . . . እንዳንካካድ ተማምለን ነበርኮ! ምነዉ ታዲያ እኔ እያመንኩሽ አንቺ ከዳሽኝ . . . ጭጭ ያሰኘኝ ሰዉ ጭጭ ሲል አልነግርህ ብለሽ ደበቅሽኝ። ትዝብት ነዉ ኢትዮጵያ ...ትዝብት ነዉ፤ እኔ ግን . . . እኔ ግን ሰማሁ አንቺ ባትነግሪኝም የገደለህ ሞተ ብለሽ ሹክ ባትይኝም የአግአዚን አለቃ ሰማይ መጥቶ አየሁት። አዎ! ያ’ ማረኝ ብዬ ስለምነዉ “በለዉ አትማረዉ” ብሎ በአጭር ያስቀረኝን ሰዉ አጠገቤ መጥቶ አየሁት። እሰይ ብዬ ጮቤ እንዳልረግጥ ቂም በቀል አላስተማርሺኝም። እንኳን ደስ ያለሽ አንዳልል አሁንም እየሞትሽ ነዉ፤ እንዳላጽናናሽም የሞተዉ ገዳይሽ ነዉ። እስኪ ንገሪኝ ምን ልበል እማማ? እኮ ንገሪኝ ምን ላድርግ ምን ልሁን ኢትዮጵያዬ? ዳር ድንበርሽ እንዳይደፈር የልጆችሽ መብት እንዳይረገጥ ቤዛ ልሁን ብዬ ዉድ ህይወቴን ገበርኩ። ለእኩልነትሽ ከዘረኞች ጋር ተፋለምኩ። አዎ! ተፋለምኩልሽ ኢትዮጵያ! ለአግአዚ አጎንብሼ አንቺን ከማዋርድ ለዘረኞች ሰግጄ ቅድስናሺን ከማረክስ ሞት ይሻላል ብዬ ሞትኩልሽ ያአባቶቼን አደራ በግንባሬ ማተም ተወጣሁልሽ።

ታድያ ምን ቢደርግ ነዉ ኢትዮጵያዬ ... እኮ ምን ቢደረግ ምን ቢታሰብ ነዉ የገደለን የሚታሰብ። በያ ንገሪኝ እማማ ወድዶ ነዉ ወይስ ተገድዶ ህዝብሽ ላስለቀሰዉ ያለቀሰዉ። ስሚኝ ኢትዮጵያዬ እርቄሽ ብሄድም አሁንም ህመምሽ ያምመኛል፤ሲከፋሽ ይከፋኛል ጣረሞትሽ ይለበልበኛል። ሆኖም . . . ሆኖም ልጆችሽን የገደለ ሰዉ ሞተ ብለሽ ስታለቅሺ ይቆጨኛል፤ ግንባሬን ላደቀቀ ከሀዲ ደረትሽን ስትደቂ ያንገበግበኛል።

ምነዉ ኢትዮጵያዬ! ምንድነዉ ችኮላዉ ለምንድነዉ ጥድፍያዉ? የፈሰሰዉ ደሜ ቀለሙ ሳይጠፋ፤ “ኡኡ” ብላ ያቀፈችኝ እናቴ እንባዋ ሳይደርቅ ለምንድነዉ አገር ተሰብስቦ ያለቀሰዉ? በይ እኮ ንገሪኝ ኢትዮጵያ ምንድነዉ ያ’ ሁሉ ዋይታ? ለእኔ ከሆነ ያለቀስሺዉ. . . . ለእኔ ከሆነ ለተሰዋሁት እንባሺን ያፈሰስሺዉ . . . እዉነቱን ንገሪኝ እማማ ዝክር ከሆነ የተወጣሺዉ። የ1997 ህልፈቴን ከሆነ ያስታወስሺዉ በያ ንገሪኝ ኢትዮጵያ የለም ብለሽ እንዳትዋሺኝ ሞቷል ብለሽ እንዳትረሺኝ። በወርሃ ሰኔ 97 ጾም ሳይፈታ ደም ፈሰሰ የአዲስ አበባ መንገድ የሰዉ ስጋ ለበሰ። ህዳር ሚካኤል ሳይታጠን የአበሻ ወጣት ታደነ፤ ወገን እንደባዳ ተቆጥሮ በአልሞ ተኳሽ አረር አረረ። ታድያ. . . . ታድያ ለምንድነዉ እማማ የዚህ ሁሉ መሀንዲስ የሚወደስ . . . ጨከኙ ገዳይሽ “አባት” ተብሎ ሙሾ የሚወረድለት. . . አገር ተሰብስቦ የሚለቀስለት?

ኢትዮጵያ ..... ኢትዮጵያ ወደ ታች አጎንብሼ ባየሁሽ ቁጥር አሳዘንሺኝ ጀግና የናፈቀ የፈሪ ቤት መሰልሺኝ። የታሉ የሰፈሬ ልጆች የታሉ ጓደኞቼ . . . . የታሉ “የነቢዩ እምባ” ፈስሶ አይቀርም ብለዉ ጮቤ ያሰረገጡኝ ወገኖቼ። የአባቶቼን ታሪክ ሲያስታዉሰኝ የእነ በላይን የእነ አብዲሳን ታሪክ ሲነግረኝ “አበሻ የጦር ወጌሻ” ይለኝ ነበር አባቴ ያኔ በህፃንነቴ . . . ያኔ አዎ ያኔ አግአዚ ሳያረዳዉ ሞቴን አልሞ ተኳሽ ሳይቀማዉ ህይወቴን። ታድያ የታለ ያ’ ሁሉ ወጌሻ ኢትዮጵያዬ? ምን ይጠቅማል ያንቺን ወለምታ የማያሽ ወጌሻ . . . ምን ሊበጅሽ ልጅሽ ሲገደል አገር ሲነቀል ጦር የማያነሳ አበሻ?

በይ እንገዲህ ኢትዮጵያ ለሰፈሬ ልጆች ንገሪያቸዉ ለጓደኞቼም ሹክ በያቸዉ - አድርሺ መልዕክቴን አንቺን መዉደዴን ለባንዳ አድሬ አንቺን አገሬን አለመካዴን። ያንቺን ዉርደት ከማየት ሞቴን መምረጤን ንገሪያቸዉ .... ንገሪያቸዉ ኢትዮጵያ! ለልጆችሽ ነፃነት የእኔ ግንባር መሰንጠቁን እነሱ እንዲኖሩ የእኔ ህይወት መነጠቁን። ንገሪያቸዉ ደግመሽ ደጋግመሽ እንዲገባቸዉ ነቢዩ የሞተዉ ለእናንተ ነዉ በያቸዉ።

ልጅሽ አይባል ኢትዮጵያ . . . አዎ ልጅሽ አይባል ለነፃነትሽ የማይታገል፤ ለዳር ድንበርሽ የማይጋደል ልጅሽ አይባል ሞትሺን በሞቱ የማይመክት . . . በአንድነትሽ የሚግደረደር ከወያኔ ጋር የሚደራደር። ይብለኝ ለእናንተ በያቸዉ የአገሬን ልጆች . . . ይብላኝ ለእናንተ አንገት ደፍታችሁ ለምትገዙ . . . እኔማ . . . እኔማ ተገላግያለሁ ለእናንተ ብዬ እኔ ሞቻለሁ ግንባሬን ለአግአዚ ህይወቴን ለኢትዮጵያ ሰጥቻለሁ።

ስሚኝ ኢትዮጵያ አገሬ . . . ስሚኝ አንቺ እናቴ፤ ለአንድ ህይወቱ የሚሳሳ አንቺነትሺን የሚረሳ ልጅ ካለሽ እጁን ይዘሽ ምከሪዉ ስማ ብለሽ ንገሪዉ . . . ወያኔን ታቅፈህ ፍርፋሪ ጎርሰህ ኑር በይዉ። ኑሮ ከሆነ አጎንብሶ መኖር፤ ኑሮ ከተባለ እየተገዙ መኖር፤ ለአራጅህ ካራ አቀብል በይዉ ይህንን ከንቱ ከገዳዩ የሚያብር የሰዉ ገልቱ። አይዞህ በይዉ ኢትዮጵያ ያንን ፈሪ ለሆዱ አዳሪ . . . አይዞህ በይዉ እየበላህ ኑር በይዉ። እኔ ነቢዩ አንደሆንኩ መገዛት እንጂ ሞት አልፈራም፤ ለፈጣሪ እንጂ ለዘረኞች አልሰግድም። ጀግና ሰዉ ካጣሽ የሚሞትልሽ ቆራጥ ከጠፋ የሚሰዋልሽ አይዞሽ ኢትዮጵያ . . . . አይዞሽ እኔዉ . . . . . እኔዉ እመጣለሁ እንደገና እሞታለሁ። ንገሪዉ ኢትዮጵያ ለዚያ ለፈሪ ለፍርፋሪ . . . ነቢዩ ይመጣል በይዉ እንደገና ሊሞት እንደገና ሊሰዋ።

ስማኝ የኔ ወንድም . . . . . ስሚኝ አንቺም እህቴ ምን ያደርጋል ግርግር ምን ይበጃል ጋጋታ? ኢትዮጵያችን በቃት የወሬ ቱማታ! አዎ! በቃት ሴረኛ፤በቃት ዘረኛ በቃት ጉበኛ . . . ኢትዮጵያችን በቃት እሷ እየሞተች እሱ የሚተኛ። ተነስ ወንድሜ ይብቃህ እንቅልፉ፤ አንቺም ተነሽ እህቴ ተደጋገፉ። በተለይ እህቴ ጠጋ ብለሽ ስሚኝ አንቺጋ ነዉና ብልሀቱ ፤”በርታ በይዉ” ወንድምሽን ጉልበት ሁኚዉ አንደ ጣይቱ። እቱ . . . እቱ ተነሺ . . . እቱ መላ ምቺ፤ ተኝቷል ወንድምሽ ቀስቅሺዉ . . . . ተነስ በይዉ፤ ወንድም ጋሻ ብለሽ ምከሪዉ፤ እጁን ይዘሽ ቃል አስገቢዉ የነቢዩን ትንቢት ንገሪዉ . . . ንገሪዉ የነቢዩን ትንቢት . . . . ነቢዩ ሞቶ አይቀርም በይዉ . . . . የነቢዩ እንባ አግአዚን ማጠቢያ እንዶድ ነዉ በይዉ . . . . እንዶድ ነዉ በይዉ. . . . . እንዶድ ነዉ በይዉ. . . . እንዶድ ነዉ በይዉ።

## በእብሪተኛው የወያኔ አገዛዝ የተፈናቀሉ ኢትዮጵያዊያን ከሁለት ሰው በላይ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አሁን ደግሞ ይግረማችሁ ብሎ ለችግራችን ተወያይተን መፍትሄ እንኳን እንዳንሻ ከሁለት በላይ ሆናችሁ መነጋገር አትችሉም በማለት የግፉን መጠን በላይ በላዩ እየደረበብን ይገኛል በመሆኑም በሃገራችን መጠለያ የማግኘት መብት ከተነፈግን፣ ሁለት ሆነነ መነጋገር ከተከለከልን፣ በግፍ ከተደበደብን፣ ልጆቻችን ለሞት አደጋ እንዲጋለጡ ከተደረጉ እንደምን የዚች ሀገር ዜጎች ነን ማለት እንችላለን? ያሉት ተፈናቃዮች የትም ብንሄድ ከዚህ የባሰ ነገር ስለማይመጣ ዜጎቹ መሆናችንን የሚቀበል መንግስት እስኪመጣ ወደ ሌላ ማንኛውም ሀገር ለመሰደድ ወስነናል በማለት አብራርተዋል።

አንዲት እናት በበኩላቸው ይሄን ሁሉ ገንዘብ የሚያግበሰብሱት መቼ ሊበሉት እንደሆን አላውቅም፤ቤታችንን በላያችን ላይ በማፍረስ አውላላ ሜዳ ላይ የጣሉን መሬቱን ለመሸጥ ነው፤ እኔ የሚገርመኝ ከመለስ እንኳን አይማሩም፤እሱ ይሄው ከሰበሰበው ጥቂቱን እንኳን ሳይበላ አፈር ገባ፤ድሃን ቢንቁትም አምላክ አለው፤ የሱ ፍርድ የመጣ ቀን መግቢያ ይጠፋል፤ እናም ያከፉ ቀን ሳይመጣ እባካችሁ ግፍ ይብቃችሁ፤ስግብግብነት ይብቃችሁ፤ለወገኖቻችሁ አስቡ በልልኝ እንዳሉት ዘጋቢያችን ገልጿል።

በዚህ የሰሞኑ የቤት ማፍረስና ዜጎችን ሜዳ ላይ የመጣል ዘመቻ ከሰባ ሺህ በላይ ዜጎች መፈናቀላቸው፣መደብደባቸውና ሜዳ ላይ መበተናቸው መዘገቡ ይታወሳል።

## አሮሚያ ዉስጥ በሙስና የከበረው ዳኛ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሆኖ ተሾመ

ባለፈዉ አርብ ህዳር 20 ቀን 2005 ዓም አመታዊ ጉባኤዉን ሲያጠናቅቅ የ77 ዳኞችን ሹመት ያጸደቀዉ  የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት አንድ ከዚህ ቀድም በክልሉ በዳኝነት ስራ ላይ የተሰማራንና የተረጋጋጠ የሙሰኝነት ታሪክ ያለበትን ዳኛ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት አድርጎ መሾሙን አዳማ የሚገኘዉ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ከስፍራዉ በላከልን ዜና ገለጸ። ይህ ከተለያዩ የምክር ቤቱ አባላት ከፍተኛ ተቃዉሞ እየቀረበበት የከፍተኛዉ ፈርድ ቤት ፕሬዚዳንት እንዲሆን የተመረጠዉ ፍቅሩ አያና የተባለዉ ግለሰብ ከዚህ ቀደም በዳኝነት ባገለገለባቸዉ የኦሮሚያ አካባቢዎች ሁሉ ህዝብ በሙሰኝነቱ እጅግ የሚጠላዉ ቢሆንም የፓርቲዉ ከፍተኛ አመራሮች ስለፈለጉት ብቻ እንዲሾም መደረጉን ዘጋቢያችን  የኦህዴድ ምንጮችን ጠቅሶ የላከልን ዜና ያስረዳል።

 የፍቅሩ አያና ስም በእጩነት ለምክር ቤቱ እንደቀረበ የምክር ቤቱ አባላት ካቀረቧቸው የመቃወሚያ ሀሳቦች መካከል ግለሰቡ በሙስና የተዘፈቀ ነው፣ በዳኘነት ስራ በተመደበበት ዞኖች ሁሉ በህዝብ የተጠላና ህዝብን ያንገላታ ነዉ ፣ የስነምግባር ችግር አለበት፣ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የለውም የሚሉ ትችቶችና አስተያየቶች ይገኙበታል። ሆኖም ይህ ሁሉ ተቃዉሞ ከምክር ቤቱ አባላት እየተሰማ የክልሉ ባለስልጣናት ጥያቄያችሁንና አስተያየታችሁን አጣርተን መልስ እንሰጣለን የሚል የተደፋፈነ መልስ በመስጠት ሹመቱ እንዲጸድቅ አድርገዋል።  የወያኔ አገዛዝ ማንም ይሹም ማን የሚገድደዉ የብሔር ብሔረሰቦች ኮታ መሟላቱ እንጂ የሚሾመዉ ሰዉ የሞራል ብቃትና በህዝብ ዘንድ ያለዉ አመኔታ በፍጹም ስለማይገደዉ ዛሬ አገሪቱ ዉስጥ በዬትኛዉም የስልጣን እርከን ላይ የሚገኙ ባለስልጣኖች ህዝብን የሚያገለግሉ ሳይሆን ህዝብን የሚዘርፉ የለየላቸዉ ሌቦች መሆናቸዉ የአደባባይ ሚስጥር ነዉ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በእለቱ የተካሄደዉ የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ጉባኤ ማጠናቀቂያ ላይ የክልሉን ፕሬዚዳንት አለማየሁ አቶምሳን ጨምሮ ብዙ የክልሉ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ከስልጣናቸዉ እንደሚነሱ አጀንዳ የተያዘ ቢሆንም ለግዜዉ ይህ ነዉ ተብሎ ባልታወቀ ምክንያት አጀንዳው እንዲሰረዝ ተድርጓል። ከክልሉ የሚደርሱን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት  በህምም የሚሰቃየዉን የክክሉ ፕሬዚዳንት አለማየሁ አቶምሳን ለመተካት ሀሳብ ቢቀርብም እሱን በሚተካው ሰው ላይ የስራ አስፈጻሚዉ ኮሚቴ አባላት መስማማት ባለመቻላቸው አለማየሁ አቶምሳ ስልጣኑን እንደያዘ እንዲቀጥል ተደርጓል። ይህ ዉሳኔ እንደተሰማ የስብሰባዉ አዝማሚያ ያልጣማቸዉ አንዳንድ የስራ አስፈጻሚዉ ኮሚቴ አባላት ስብሰባዉን ረግጠው የወጡ ሲሆን ስብሰባዉ ሲጀመር ከነበሩት ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣኖች ዉስጥ ከምክትል ፕሬዚዳንቱ ከአብዱላዚዝ በስተቀር ፕሬዚዳንቱን ጨምሮ ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በማጠቃለያው ጉባኤ ላይ አንዳልተገኙ ለማወቅ ተችሏል።

## የመከረኛዉ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ክስ እንደገና ተቀሰቀሰ

ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቸኛ የግል ጋዜጣ የነበረችዉ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆነዉ ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ ከዚህ ቀደም በፌዴራል ዐቃቤ- ሕግ ቀርቦበት የነበረው የፈጠራ ክስ እንደገና ተቀስቅሶ ፍርድ ቤት መመላለስ መጀመሩን ከአዲስ አበባ የደረሰን ዜና አስረዳ። በለፈዉ ሀሙስ ህዳር 20 ቀን 2005 ዓም የፍርድ ቤት መጥሪያ የያዙ የፖሊስ አባላት ተመስገንን ፍለጋ ጋዜጣዉ ቢሮ ድረስ የመጡ ቢሆንም ጋዜጠኛ ተመስገን ከአዲስ አበባ ውጪ መሆኑ ተነግሯቸው ወደ መጡበት ተመልሰዋል።

በማግስቱ ዓርብ ህዳር 21 ከሰአት በኋላ የፌዴራል ፍተኛው ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 16ኛ ወንጀል ችሎት ጋዜጠኛ ተመስገን በሌለበት ችሎት የሰየመ ሲሆን የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ለተመስገን ለማድረስ የሄዱት ፖሊሶች በጊዜው ሊያገኙት አለመቻላቸውንና ፍርድ ቤት ለጥያቄ እንደሚፈልገዉ  ለሥራ ባልደረቦቹ መንገራቸውን ለፍርድ ቤቱ ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም ለጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ የዋስትና መብት የነፈጉት ዳኛ መጥሪያው እንዳልደረሰው ካረጋገጡ በኋላ ዐቃቤ-ህጉን የውሳኔ አስተያየት የጠየቁ ሲሆን ዐቃቤ- ህግም ክሱ በቀጣይ እንዲቀርቡልኝ ማዘዣ ይጻፍልኝና አጭር ቀጠሮ ይሰጠኝ  የሚል ማብራሪያሰጥቶ ሰጥቷል፡፡ የችሎቱ ዳኛም በበኩላቸው የፍርድ ቤት መጥሪያ ለፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝና ለድርጅቱ ጠበቃ እንዲደርስ ማዘዣ እንዲወጣ አዘው ለታህሳስ 2 ቀን 2005 ዓ.ም ቀጣይ ቀጠሮ ሰጥቶ በእለቱ የዋለዉ ችሎት ተዘግቷል።

የፍትህ ጋዜጣ ህትመት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተዘጋ ሲሆን "ነፃ ጋዜጣ ወይም ሞት" ብሎ የወያኔን ፀረ ፕሬስና ፀረ ነጻ ሀሳብ አምርሮ የሚታገለዉ ተመስገን ደሳለኝ "አዲስ ታይምስ" የሚል መጽሄት መጀመሩ አይዘነጋም።  ከመለስ ዜናዊ ሞት በኋላ በነበሩት ባለፉት ሦስት ወራት ኢትዮጵያ ዉስጥ የፕሬስ ነፃነት ይሻሻላል የሚል እምነት የነበራቸዉን አንዳንድ የዋሆችን ሀ/ማርያም ደሳለኝ ገና ከመድረሱ ልክ አለመሆናቸዉን በተግባር እያሳያቸዉ ነዉ ሲሉ አንድ አስተያየት ሰጪ ከአዲስ አበባ ለዝግጅት ክፍላችን ስልክ ደዉለዉ ተናግረዋል።

## የለገጣፎ ነዋሪዎች እኛ ያልመረጥነው ከንቲባ አያስተዳድረንም

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የዘረኛው አገዛዝ ባለስልጣናት አዲሶቹን ተሻሚዎች አንቀበልም ካላችሁ ከጀርባችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች አሉ ማለት ነው፣ ብትቀበሉ ይሻላችሁዋል በማለት ለማስፈራራት ቢሞክሩም ህዝቡ ግን አሻፈረን ማለቱን ኢሳት ዘግቧል።

ህዝቡን ይበልጥ ያስቆጣው ሌላው ጉዳይ ደግሞ በሙስና ተገምግሞ የወረደው ምክትል ከንቲባ ተመልሶ ወደ ቦታው እንዲቀመጥ መደረጉ ሲሆን የፍትህ ሚ/ር ሚ/ር ዲኤታ የሆነው ብርሀኑ ጸጋየ የቀድሞው ከንቲባና ባልደረቦቹ በህግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ገልጾ የነበረ ቢሆንም፣ በግለሰቦቹ ላይ እስከአሁን ምንም አይነት ክስ አለመቅረቡ ነዋሪዎችን አበሳጭቷል ብሏል ኢሳት በዘገባው።

ከአዲስ አበባ ከተማ በሰሜን ምስራቅ በኩል 21 ኪሎሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው የለገጣፎ/ለገዳዲ ከተማ በኦሮሚያ ክልል በፊንፊኔ ልዩ ዞን ሥር በከተማ አስተዳደርነት እንድትመሰረት መደርጉ ይታወሳል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ**:- በ 358 MB, በ 837 kHz
**አጭር ሞገድ**:- በ 31 MB  በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።  g7radio@ginbot7.org